**በኢትዮጵያ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ህብረት /ኢደኃኅ/**

**በኦሮሞ ፌዴራሊስት ዲሞክራሲያዊ ንቅናቄ /ኦፌዴን/**

**በሶማሌ ዲሞክራሲያዊ ኃይሎች ቅንጅት /ሶዴኃቅ/**

**በዓረና ትግራይ ለዲሞክራሲና ለሉአላዊነት /ዓረና/**

**በአንድነት ለፍትህና ለዲሞክራሲ ፓርቲ /አንድነት/**

**በኢትዮጵያ ዲማክራሲያዊ አንድነት ንቅናቄ /ኢዴአን/**

**ከተጀመረው**

**መድረክ ለዴሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ /መድረክ/ በሀገራችን ወቅታዊ ሁኔታ ላይ የተሰጠ መግለጫ**

በሃገራችን፣ ኢትዮጵያ ባለፉት አስራ ሰባት ዓመታት ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ በተደረገው ትግል ውስጥ በርካታ ተቃዋሚ የፖለቲካ ድርጅቶች ወደ ፖለቲካ መድረኩ ብቅ ማለታቸውና የነዚህን የተቃዋሚ ፓርቲዎች ትግል ለማስተባበር ይቻል ዘንድም በርካታ የትብብር ጥረቶች መደረጋቸው ይታወሳል፡፡ የተደረጉት ጥረቶች ሰምረው በሃገራችን የታሰበውን ግብ ለመምታት ባያበቁም፣ ለወደፊት የሰመረ ትብብር ለመፍጠር ይቻል ዘንድ ጠቃሚ ልምዶች ማስገኘታቸው አሌ የማይባል ሀቅ ነው፡፡ መድረክ ለዲሞክራሲያዊ ምክክር በኢትዮጵያ/መድረክ/ የተባለውን ስብስብ ስድስት የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ሁለት ታዋቂ የፖለቲካ ሰዎች በሰኔ ወር 2000 ዓ.ም ላይ የጀመሩትም ይህንን እውነታ ተገንዝበው ነው፡፡

የተሳካ ዴሞክራስያዊ ለውጥ ማምጣት ይቻል ዘንድ ተቃዋሚ የፖለቲካ ፓርቲዎች በጋራ ፕሮግራም ዙሪያ ትግላቸውን ማስተባበር እንዳለባቸው መድረኩ ቢያምንም፣ እዚያ ለመድረስ መጀመሪያ በተወሰኑ መርሆችና ግቦች ዙሪያ ሊሰባሰብ የሚችለውን ሀይል የማሰባሰብን እና በዚሁ ጥላ ስር ሆኖ ለሚቀጥለው ስራ አስፈላጊ የሆኑትን ቅድመ ዝግጅቶች እያከሄዱ የመቆየትን ስልት መርጦ በዚሁ መሠረት ሲንቀሳቀስ ቆይቶአል፡፡ በዚህም መሠረት ታህሣሥ አስራ ስምንት እና ሃያ አምስት 2001 ዓ.ም፣ በኢምፔርያል ሆቴል ባካሄደው የሁለት ቀናት አውደ ጥናት ላይ ሕዝብን አወያይቶአል፡፡

መድረኩ ከዚህ ሌላም የተጀመረውን ስብስብ ማስፋት ይቻል ዘንድ ከተቀመጡት መርሆችና መመዘኛዎች አኳያ መድረኩን ሊቀላቀሉ ይችላሉ ያላቸውን እና ለመቀላቀል ፈቃደኛ ከሆኑ ድርጅቶች ጋር ግንኙነት እና ምክክር ሲያካሄድ ከቆየ በኋላ ቀደም ሲል መድረኩን ከተቀላቀሉት ፓርቲዎች በተጨማሪ፤

1. አንድነት ለፍትህና ለዴሞክራሲ ፓርቲ (አንድነት)
2. የኢትዮጵያ ዴሞክራስያዊ አንድነት ንቅናቄ (ኢዴአን) መድረኩን ተቀላቅለዋል፡፡ ይህም ለመድረኩ መጠናከር ተጨማሪ ግብአት ሆኖ ትግሉን አንድ እርምጃ ወደፊት እንደሚገፋው መድረኩ ፅኑ እምነት አለው፡፡

እነዚህን ማሳካቱን ተከትሎ የመድረኩ 4ኛ ጉባኤ አቶ ገብሩ አስራትን የወቅቱ የምክክር መደረኩ ሊቀ መንበር፤ የተከበሩ አቶ ኤርሜፎ ኤርድሎን ዋና ፀሐፊ እንዲሆኑ ከመምረጡም ባሻገር አንድ ግብረ ሃይልም አቋቁሟል፡፡ ግብረ ሃይሉ ከእያንዳንዱ ፓርቲ አንድ የአመራር አባልና ሁለቱ ግለ ሰብ የመድረኩ አባላት ያሉበት ሆኖ የድርጅቶቹ ተወካዮች ከፓርቲዎቻቸው ጋር እየመከሩ በሚያካሂዱት ውይይትና ድርድር የመድረኩ አባላት የሚስማሙባቸውን የጋራ እምነቶችንና አቋሞችን ለይቶ በማውጣት እና በዚሁ ላይም በመንተራስ ወደፊት መድረኩ በፓርቲዎች አዋጅ መሠረት ለሚፈጥረው የትብብር ደረጃ የሚሆን ማኒፌስቶ ያዘጋጃል፡፡

መድረኩ በ4ኛ ጉባኤው ሰሞኑን በመንግስት ባለስልጣናት በተሰጡት መግለጫዎች እና ሲካሄዱ በሰነበቱት ስብሰባዎች ላይ በማተኮር በወቅታዊ ፖለቲካዊ እና ኢኮኖምያዊ ጉዳዩች ላይም ተወያይቷል፡፡ በፖለቲካው ዙሪያ በተለይ ለፖለቲካ ምህዳሩና ለአገር ደህንነት ትኩረት ሰጥቷል፡፡ ጉባኤው ከተመለከታቸው የፖለቲካ ጉዳዮች ውስጥ የአንድነት ለዴሞክራሲ እና ለፍትሕ ፓርቲ ሊቀ መንበር የሆኑት የወ/ሪት ብርቱካን እና የሌሎች ኢትዮጵያዊያን የፖለቲካ እስረኞች ጉዳይ፤ በፕሬስ አባላት ላይ እየተፈፀመ ያለው እስር እና በክስ አሳቦ በየችሎቱ የማጉላላትና የማንከራተት ዘመቻ፤የመከላከያ ሰራዊታችን ከሶማልያ መውጣት እና ገዢው ፓርቲ በወጣቶች ላይ ይዞት ያለው የፖለቲካ ቅስቀሣ ዘመቻ ይጠቀሳሉ፡፡ መድረኩ ታህሣሥ 26 ቀን 2001 ዓ.ም. ባስራጨው መግለጫ እንደተመለከተው ሁሉ የወ/ሪት ብርቱካን ዳግም መታሰር በሽምግልና ተፈቷል የተባለለትን ጉዳይ ወደ ኋላ የሚመልስ፤ ሃሳብን በነፃ የመግለፅ መብትን የሚጥስ እና ሕግንና ስርዓትን ያልተከተለ እርምጃ መሆኑን በድጋሚ ይገልጣል፡፡ የእርሳቸው ቃል በታፈነበት ሁኔታ እርሳቸውን ጥፋተኛ

ለማሰኘት እየተደረገ ያለውን ቅስቀሳም ያወግዛል፡፡ መድረኩ እንደዚሁ በጋዜጠኞች ላይ እየደረሰ ያለው ወከባ ባስቸኳይ እንዲቆምም አበክሮ ይጠይቃል፡፡

እነዚህ እና እነዚህን የመሳሰሉት የመብት ጥሰቶች የተበራከቱት በቅርቡ ፕሬስን፣ ፓርቲዎችን እና ሲቪክ ማህበራትን የሚመለከቱት ሕጎች መፅደቃቸውን ተከትሎ መሆኑን፤ ለምርጫ 2002 የቀረው ጊዜ ጥቂት ወራት ከመሆኑ አንፃር
እነዚህ እርምጃዎች የኢህአዴግ መንግስት ምህዳሩን በማስፋት ፈንታ ተፃራሪውን ስራ እየሰራ መሆኑን ያመለክታሉ፡፡ የምክክር መድረኩ እነዚህ አሉታዊ ተግባሮች ተወግደው የፖለቲካ ምህዳሩ ለምርጫ የተመቻቸ ይሆን ዘንድ ከወዲሁ መወሰድ ያለባቸው እርምጃዎች እንዲወሰዱ አበክሮ ይጠይቃል፡፡ መድረኩ በፖለቲካ ፓርቲዎች ምዝገባ አዋጅ ቁጥር 573/2000 መሠረት ራሱን ወደ ጠንካራ አደረጃጀት ለማሸጋገር የጀመረው ስራ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የሚመጣው ምርጫ የተሳካ ይሆን ዘንድ መከናወን አለባቸው የሚላቸውን ተግባራት ለመለየት እና በዚሁ ዙሪያ ከመንግስት እና ከገገርው ፓርቲ ጋራ ለመደራደር ቅድመ ዝግጅት እያደረገ መሆኑን ከወዲሁ ለማሳወቅ ይፈልጋል፡፡

የምክክር መድረኩ የመከላከያ ሠራዊታችን የሶማሊያን ምድር ለቆ ወደ ሃገሩ መመለሱን በደስታ ይቀበለዋል፡፡ ከሃገሩ እና ከቤተሰብ ርቆ የቆየውን ሠራዊታችንን በአክብሮት መቀበልና መያዝ ይገባል ብሎም ያምናል፡፡ ይህ እንደተጠበቀ ሆኖ፤ ከዚህ ሁሉ አላስፈላጊ የህይወት መስዋእትነት እና የአገር ሃብት ብክነት በኋላም ቢሆን፤ የሶማልያ ሁኔታ ከሁለት ዓመት በፊት ከነበረው ሁኔታ በመሰረቱ አለመለወጡ፤ የተወሰደው የጣልቃ ገብነት እርምጃ አላስፈላጊ እንደነበር ማንኛውም የህዝብ ግንኙነት ስራ ሊሽረው የማይችል በአለት ላይ የተፃፈ እውነታ ሆኖአል፡፡

መድረኩ ከሁለት ዓመት በፊት ብቅ ያለውን እና እስካሁን ድረስ ሊረግብ ያልቻለውን የሃገራችንን ኢኮኖምያዊ ቀውስ እና ተያያዥ ጉዳዮችንም ተመልክቷል፡፡ አምና በመንግስት እና በእርዳታ ሰጪዎች መሃከል በተረጂዎች ብዛት ዙርያ የተከሰተው እሰጣ ገባ ያስታውሷል፡፡ ይህ አሃዝ አሁንም እንደተሰቀለ ሆኖ በሚልዮን የሚቆጠሩ ዜጎችን የረሃብ ሰለባ አድርጓቸው ይገኛል፡፡ የዋጋ ውድነቱ ከፍተኛ ነው የሚል መግለጫ አልበቃ ብሎት ከዚምባቡዌው ቀጥሎ የሚጠራ የኑሮ ውድነት እየተባለለት ነው፡፡ የኢህአዴግ መንግሥት እየተከተለ ያለው የኢኮኖሚ ፖሊሲ በሁሉም የሕብረተሰብ ክፍሎች በተለይ ደግሞ በወጣቱ ላይ እየፈጠረ ያለው የስራ አጥነት እና የተስፋ መቁረጥ ሁኔታ እጅጉን የከፋ አድርጎታል፡፡ እነዚህን ወጣቶች ኢሕአዴግ ምርጫ 97 ላይ ሺዎችን እንዳላሰራቸው ሁሉ ተደራጅታችሁ እኔን ከደገፋችሁ በጥቃቅን እና አነስተኛ ተቋማት በኩል ስራ የምታገኙበትን መንገድ እፈጥርላችኋለሁ እያለ ወጣቱን የማባበል እና የማዘናጋት ዘመቻ እያካሄደ ነው፡፡ ዳሩ ግን

የኢትዮጵያ ወጣቶች ለጨቋኝ ገገሮች መቼውንም ተንበርክከው ስለማያውቁ በዚህ ቅስቀሳ ቀበቶአቸውን እንደማያላሉ መድረኩ ፅኑ እምነት አለው፡፡

በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ በዚሁ ላይ አለማቀፋዊው የኢኮኖሚ ቀውስ ያስከተለው ጫና በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ክፉኛ እየደቆሰን ነው፡፡ ከተጫነብን ደካማ እና ብልሹ የፖለቲካ ስርዓት እና ካለብን አስከፊ ድህነት አኳያ እንደዚህ ያለ አዲስ እና አሳሳቢ ክስተት መጨመሩ መድረኩን እጅግ ያሳስበዋል፡፡ ኃላፊነትና ተጠያቂነት የሚሰማቸው መንግስታት ሁኔታውን በፅሞና ገምግመው መሰረታዊና ሁሉን አቀፍ እርምጃዎች እየወሰዱ ቢሆንም የኢህአዴግ መንግስት ግን በእንግሊዘኛ መግለጫው ቅድመ ሁኔታዎችን እርግፍ አድርጋችሁ እርዳታችሁን ይዛችሁ ቶሎ ካልደራሳችሁልን በርካታ የአፍሪካ መንግስታት የከሸፉ መንግስታት እንሆንባችኋለን ሲል በአማርኛው ደግሞ አለማአቀፋዊ ቀውሱን እንደ መልካም አጋጣሚ በመውሰድ ከችግሩ ለማምለጥ ይቻላል ይለናል፡፡ ከዚህም አልፎ ኢኮኖሚያችን አሁንም በፍጥነት አድጓል እያለ አሃዞችን እየጠቀሰልን ነው፡፡ ይባስ ብሎም ሚልየነር ገበሬዎች ተፈጥረዋል በማለት በአገራችን አርሶአደር ድህነት፣ ረሃብና ሰቆቃ ላይ ከማሾፍ ያልተናነሰ የሕዝብ ግንኑነት ስራ እየሰራ ነው፡፡ እነዚህ እውነታዎች የሚያመለክቱት የኢህአዴግ መንግስት የተደቀኑብንን ችግሮች መፍታት ይቅርና በትክክልም ለመገንዘብ እንዳይችል ይዞት ያለው የአብዮታዊ ዴሞክራስያዊ መስመር እጅጉን የሚገድበው መሆኑን ነው፡፡

እስካሁን ከተጠቀሱት ኩነቶች በተጨማሪ በአንድ ወቅት ሲቪል ሰርቪስ ሪፎርም ሰሞኑን ደግሞ መሰረታዊ የስራ ሂደት ለውጥ (ቢ.ፒ.አር.) በሚል የሚጠራው ሲቪል ሰሪቪሱን እያወከ ያለው ዘመቻ እየተስተዋለ ነው፡፡ ቢ.ፒ. አር በሚል ሽፋን የገዢው ፓርቲ አባል ያልሆኑትን ዜጎች ከስራ እና ከኑሮ እያፈናቀሉ ያለብቃታቸው ለውድድር ባልተከፈተ መልኩ የፓርቲ አባሎችን በመሰግሰግ ሲቪል ሰርቪሱን ወደ ፓርቲ መዋቅርነት ለመቀየር እየተደረገ ያለው ሩጫ ቆሞ፤ የሲቪል ሰረቪስ ቅጥር ለማንኛውም ዜጋ በዜግነቱና በሙያዊ ብቃቱ ብቻ የሚደርስ አገርን የሚያገለግሉበት እና ሰርተው የሚጠቀሙበት እንዲሆን መድረኩ አጥብቆ ይጠይቃል፡፡

ሰሞኑን የገዢው ፓርቲ ሽር ጉድ ከታየባቸው ጉዳዮች አንዱ ለአፍሪካ የእርስ በርስ መገማገሚያ መድረክ እንዲቀርብ በአንድ መንግስት በመለመለው የአማካሪ ቡድን በተዘጋጀው ሠነድ ላይ ለመወያየት የተጠሩት ስብስባዎች ነበሩ፡፡ በእነዚህ ስብሰባዎች ላይ የተገኙ የመድረኩ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ተወካዮችም በተገኙባቸው ስብሰባዎች መንግስት አጥጋቢ ስራ ተሰርቷል ብላችሁ መስክሩልኝ በማለት ተሰብሳቢዎችን ሲወተውት ትክክል አለመሆኑን በገሃድ ተሟግተዋል፡፡ መድረኩ ይህ የተዘጋጀው የግምገማ ሠነድ ህዝብ በጥልቀት ያልመከረበትና ያለውን የአገራችንን ተጨባጭ

ሁኔታ የማያንፀባርቅ ሰነድ መሆኑን ለሚመለከተው ሁሉ እየገለፀ ለወደፊት በዚሁ ጉዳይ ላይ ሰፋ ያለ መግለጫ የሚያወጣ መሆኑን ከወዲሁ ይገልፃል፡፡

በመጨረሻም የመድረኩን መጀመር በበጎ ለተቀበሉትና በሞራል ድጋፋቸውን ለሰጡ ሁሉ መድረኩ ምስጋናውን ያቀርባል፡፡ ይህን አስቸጋሪ በሆነ ሁኔታና የኢትዮጵያ ህዝብ አሸናፊነት ላይ ተማምኖ የተጀመረውን የመድረክ እንቅስቃሴ በተቻላቸው እንዲደግፉ መድረኩ መላ ኢትዮጵያውያንን ይጠይቃል፡፡ መድረኩን የጀመሩት ፓርቲዎች አባላት እና ደጋፊዎችም ፓርቲዎቻችሁ ይህንን መድረክ እንዲቀላቀሉ እና እንዲያጠናክሩ ላደረጋችሁት ትግል እያመሰገነ አሁን መድረኩ እየገባበት ያለውን ስራ ክብደትና ፋይዳ በውል በመገንዘብ አንድ ጠንካራ እና ሁሉንም ሐቀኛ ተቃዋሚዎች ሊያሰባስብ የሚችል ጥምረት ይወጣ ዘንድ መድረኩ ለሚያደርገው ጥረት የተለመደው ድጋፋችሁ እንደማይለየው እምነቱ ጽኑ ነው፡፡ የኢህአዴግ አባላትና ደጋፊዎችም ብትሆኑ ይህ እንቅስቃሴ ለአገራችን ሌላ አመራጭ ለማቅረብ ተብሎ የሚደረግ እንቅስቃሴ እንጂ በማንኛውም መልኩ ኢህአዴግን ለማጥፋትና የአባላቱን መብት ለማሳነስ የታለመ እንቅስቃሴ ያለመሆኑን ተገንዝባችሁ ፓርቲያችሁ የበኩሉን አወንታዊ አስተዋፅኦ ያደርግ ዘንድ የበኩላችሁን ገንቢ ሚና እንድትጫወቱ መድረኩ ታሪካዊ ጥሪውን ያቀርባል፡፡

ሠላማዊና ሕጋዊ ትግላችን ተጠናክሮ ይቀጥላል!!!

አዲስ አበባ

የካቲት 12 ቀን 2001 ዓ.ም.